የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አስራ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፭
አዲስ አበባ-ታህሣስ ፳፫ ቀን ፪ሺ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No. 5
ADDIS ABABA-2nd January, 2008


## ማውጫ


ደንብ ቁጥር ፩፻፵፪/፪ሺ፻

የአፍሪካ የእርስ በርስ መገማገሚያ ስልትን በኢትዮጵያ ተግባራዊ ለማድረግ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ...................... ገጽ ፫ሺ፱፻፷፰


## CONTENTS


Regulation No. 142/2008

The Council of Ministers Regulation to Provide For The Implementation of African Peer Review Mechanism In Ethiopia ...................... Page 3968


ደንብ ቁጥር ፩፻፵፪/፪ሺ፻

## የአፍሪካ የእርስ በርስ መገማገሚያ ስልትን በኢትዮጵያ ተግባራዊ ለማድረግ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ «የአፍሪካ የርስ በርስ መገማገሚያ ስልትን በኢትዮጵያ ማስፈጸሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፵፪/፪ሺ፻» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ፤

፩. «የአፍሪካ የርስ በርስ መገማገሚያ ስልት» ማለት የኢዲስ አጋርነት ለአፍሪካ ልማት የዘረጋውና ኢትዮጵያን ጨምሮ ፈቃደኛ የሆኑ የአፍሪካ ህብረት አባል አገራት ተቀብለው ራሳቸውን የሚቃኙበት ስልት ነው፤

፪. «ምክር ቤት» ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ መሠረት የተቋቋመው የአፍሪካ የርስ በርስ መገማገሚያ ስልት ብሔራዊ ምክር ቤት ነው፤

፫. «ዋና ዋና ባለድርሻዎች» ማለት በአፍሪካ የርስ በርስ መገማገሚያ ስልት ሂደት ሰፊውን ባለድርሻዎች እንዲወክሉ ታስቦ በምክር ቤቱ ውስጥ መቀመጫ የተሰጣቸው ባለድርሻዎች ናቸው፤

፬. «ገምጋሚ ተቋም» ማለት በአፍሪካ የርስ በርስ መገማገሚያ ስልት የግምገማ ዘርፎች መሠረት የኢትዮጵያን የራስን በራስ ግምገማ አካሂዶ ረቂቅ ሪፖርት የሚያቀርብ ተቋም ወይም ሰው ነው፤

Council of Ministers Regulation No. 142/2008

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE IMPLIMENTATION OF AFRICAN PEER REVIEW MECHANISM IN ETHIOPIA

This Regulation is issued by the council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005.

1. *Short Title*

   This Regulation may be cited as the "Implementation of African Peer Review Mechanism in Ethiopia Council of Ministers Regulation No. 142/2008".

2. *Definitions*

   In this Regulation:

   1/ "African Peer Review Mechanism" means the self-monitoring mechanism for African states initiated by the New Partnership for Africa's Development and voluntarily acceded to it by member states of the African Union, including Ethiopia;

   2/ "Governing Council" means the National governing council for African Peer Review Mechanism established under Article 5 of this Regulation;

   3/ "Key Stakeholders" means those interested groups who are selected to the Governing Council to provide for stakeholders the wider representation in the African Peer Review Mechanism Process;

   4/ "Technical Research Institution" means a body or a person that undertakes the Ethiopian country self assessment and submits a draft report on the same based on the thematic areas of the African Peer Review Mechanism;


ያንዱ ዋጋ Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ ፩
Negarit G. P.O. Box 80,001

፭. «የአፍሪካ የርስ በርስ መገማገሚያ ስልት የግምገማ ዘርፎች» ማለት የራስን በራስ ግምገማ የሚደረግባቸው የዲሞክራሲ፣ የኢኮኖሚ፣ የኮርፖሬትና የማኅበራዊ-ኤኮኖሚ ልማት ዘርፎች ናቸው፤

፮. «ብሔራዊ መርሃ - ግብር» ማለት ከራስን በራስ ግምገማ ሪፖርት በመነሳት ደካማ ጎንን ለማስተካከልና ምርጥ አሠራሮችና ፖሊሲዎችን ለመተግበር የሚቀርበው የመጨረሻው ፕሮግራም ነው፤

፯. «የአፍሪካ የርስ በርስ መገማገሚያ ፓነል» ማለት በአፍሪካ ደረጃ የተቋቋመው የታዋቂ ሰዎች ስብስብ ነው።

፫. ዓላማ

የዚህ ደንብ ዓላማ የአፍሪካ የርስ በርስ መገማገሚያ ስልትን ተግባራዊ በማድረግ ኢትዮጵያ የጀመረችውን የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማትና የመልካም አስተዳደር ግንባታን ማፋጠንና ጥልቀት እንዲኖረው ማድረግ ይሆናል።

፬. ተጠሪ ስለመመደብ

በአህጉር ደረጃ ከተቋቋሙት የአፍሪካ የርስ በርስ መገማገሚያ ስልት ተቋማት ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች መንግሥትን የሚወክል ተጠሪ ይመደባል።

፭. የብሔራዊ ምክር ቤት መቋቋም

፩. የአፍሪካ የርስ በርስ መገማገሚያ ስልት ብሔራዊ ምክር ቤት በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪. እንዳስፈላጊነቱ በየክልሎችም ተጠሪነታቸው ለብሔራዊው ምክር ቤት የሆኑ የባለ ድርሻዎች ምክር ቤቶች ይቋቋማሉ።

፮. የምክር ቤቱ አባላት

፩. የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር ፳፫ ሆኖ፣ ዋና ዋና ከሆኑት ባለድርሻዎች ተውጣጥተው ይሰየማሉ።

፪. ምክር ቤቱ በመንግሥት የሚሰየም ሊቀመንበር ይኖረዋል።

፯. የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩. የኢትዮጵያ የራስን በራስ ግምገማ ሂደት ከማናቸውም ተጽእኖ ነጻ የሆነና በሙያ ብቃትና ተአማኒነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን በበላይነት ይከታተላል፤

፪. በገምጋሚ ተቋም የሚቀርበውን የራስ በራስ ግምገማ ረቂቅ ሪፖርት ይመረምራል፤

፫. የአፍሪካ የርስ በርስ መገማገሚያ ስልት ፓነል የሚያቋቁማቸው የድጋፍና የግምገማ ቡድኖች በኢትዮጵያ ለምክክርና ለግምገማ ተግባር የሚያደርጉትን ጉብኝት ያመቻቻል፣ ያስተናግዳል፤

፬. ሁሉም ባለድርሻዎች ስለአፍሪካ የርስ በርስ መገማገሚያ ስልት ሂደት ግንዛቤ እንዲኖራቸውና ሙሉ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያደርጋል፤

፭. የአፍሪካ የርስ በርስ መገማገሚያ ስልት ሂደቱ ትክክለኛ መሆኑንና የሁሉንም ተሳትፎና ትብብር ያገኘ መሆኑን ያረጋግጣል፤

5/ "Thematic Areas of the African Peer Review Mechanism" means the focal areas for self-assessment that are referred to as Democratic, Economic, Corporate and Socio-economic Developments;

6/ "National Plan of Action" means the final programme resulted from the self-assessment report to rectify shortcomings in the system and fostering best practices and policies;

7/ "African Peer Review mechanism Panel" means the panel of eminent persons set at the African Continent level;

3. *Objectives*

The objective of this Regulation is to launch the African Peer Review Mechanism with a view to enhance and extend the already taken up socioeconomic development as well as building good governance in Ethiopia.

4. *Assignment of Focal Point*

The Government shall assign a representative to serve as focal point in its relations with the continental organs of the African Peer Review Mechanism.

5. *Establishment of Governing Council*

1/ The National Governing Council for African Peer Review Mechanism is hereby established.

2/ Where necessary, regional councils of stakeholders accountable to the National Governing council shall be established.

6. *Members of the Governing Council*

1/ Members of the Governing council shall be 23 in number and shall be selected from among the key stakeholders.

2/ The Governing Council shall have a Chairperson to be appointed by the Government.

7. *Powers and Duties of the Governing Council*

The Governing Council shall have the powers and duties to:

1/ oversee the process of Ethiopian country self-assessment ensures independence, professionalism and credibility;

2/ review the self-assessment reports submitted by the Technical Research Institution.

3/ arrange and facilitate the visits from assessment and support teams of the Panel of the African Peer Review Mechanism to Ethiopia for assessing and counseling;

4/ aware all stakeholders as to the African Peer Review Mechanism process and effect their full participation in it;

5/ ensure accurateness, participation and coordination in the whole process of the African Peer Review Mechanism;

፮. የራስን በራስ ግምገማ ሪፖርት ላይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ይለያል፤ የመጨረሻውን ሪፖርትና ብሔራዊ መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለመንግሥት ያቀርባል፤

፯. በጀቱ በመንግሥት ሲፈቀድ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ ሂሳቡም እንዲመረመር ያደርጋል።

፰. <u>የምክር ቤቱ ስብሰባዎች</u>

፩. ምክር ቤቱ ለሥራው ባስፈለገ መጠን ይሰበሰባል።

፪. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል።

፫. የምክር ቤቱ ውሣኔ በድምፅ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምፅ እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

፬. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

፱. <u>የሊቀመንበሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

የምክር ቤቱ ሊቀመንበር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩. የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይጠራል፣ በሊቀመንበርነት ይመራል፤

፪. የምክር ቤቱን ውሳኔዎች ተግባራዊነት ያረጋግጣል፤

፫. የራስን በራስ ግምገማ ተግባር ለማከናወን የገምጋሚ ተቋም ይቀጥራል፤

፬. የአፈፃፀም እቅድ እንዲወጣና እንዲተገበር ያደርጋል፤

፭. በጀት እንዲዘጋጅና በምክር ቤቱ ታይቶ በመንግሥት እንዲጸድቅ ያደርጋል፤

፮. የምክር ቤቱን አባላትና አጋር ድርጅቶችን ያስተባብራል፤

፯. የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት ሥራዎች በበላይነት ይከታተላል፤

፰. በየክልሉ የሚካሄደውን የአፍሪካ የርስ በርስ መገማገሚያ ስልት ሂደትና እንቅስቃሴ ያስተባብራል፤

፱. በምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፤

፲. <u>ጽሕፈት ቤት</u>

፩. ምክር ቤቱ ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለውና ለሊቀመንበሩ ተጠሪ በሆነ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚመራ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል።

፪. ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፤

ሀ) የምክር ቤቱን የአፈጻጸም ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ በሊቀመንበሩ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ) የምክር ቤቱን ፕሮግራሞችና የዕለት ተዕለት ተግባራት ያስተባብራል፤ ያስፈጽማል፤

ሐ) የምክር ቤቱን ሰነዶች ይይዛል እንዲሁም የሕዝብ ግንኙነት ሥራ ያከናውናል፤

መ) በአፍሪካ የርስ በርስ መገማገሚያ ስልት ሂደት ሕዝቡ ከፍ ባለ የባለቤትነት ስሜት ተሳትፎ እንዲያደርግ ይቀሰቅሳል፣ ግንዛቤ ይፈጥራል፤

6/ identify key areas of concern on the self-assessment report; prepare and submit to the Government the final report and the National Plan of Action;

7/ implement its budget upon approval by the Government, and orders the auditing of its accounts.

8. *Meetings of the Governing Council*

1/ The Governing Council shall meet as frequently as the conducting of its business so requires.

2/ There shall be quorum where more than half of the members of the Governing Council are present at a meeting.

3/ The Governing Council shall pass its decisions by majority vote; in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Governing Council may adopt its own rules of procedure.

9. *Powers and Duties of the Chairperson*

The Chairperson of the Governing Council shall have the powers and duties to:

1/ call meetings and preside the meetings of the Governing Council;

2/ ensure that decisions of the Governing council are implemented;

3/ appoint a technical research institution for the performance of the country self-assessment report;

4/ make sure that a work plan is prepared and implemented;

5/ order for the preparation of budget proposal to be approved by the government after it is seen by the Governing Council;

6/ coordinate stakeholders and partner institutions of the governing council;

7/ oversee the functions of the Secretariat of the Governing Council;

8/ coordinate the activities of the African Peer Review Mechanism process on the regional states level;

9/ carry out other functions as may be assigned to him by the Governing Council.

10. *Secretariat*

1/ The Governing Council shall have a Secretariat having its own juridical personality and to be headed by a chief Executive Officer accountable to the Chairperson.

2/ The Secretariat shall have the functions to:

(a) prepare plans of action and budgets of the Governing Council and implement the same upon approval by the Chairperson.

(b) coordinate and execute programs and day-to-day activities of the Governing Council;

(c) keep documentations of the Governing Council and undertake public relation activities of the Governing Council;

(d) undertake awareness creation and promotion activities to enhance public responsibility and participation in the process of the African Peer Review Mechanism;

ሠ) የምክር ቤቱን ስብሰባዎችና የመስክ ጉብኝቶች ይከታተላል፣ እንዲሁም በምክር ቤቱ ስም እንግዶችን ተቀብሎ ያስተናግዳል፤

ረ) የገምጋሚ ተቋም ሥራ የተቃና እንዲሆን ይደግፋል፣ አስፈላጊውን ሁሉ ያመቻቻል፤

ሰ) በምክር ቤቱና በሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፤

ሸ) ሂሳብ እንዲያዝ ያደርጋል፡፡

፫. ጽሕፈት ቤቱ ከተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት በትውስት የሚመደቡና ሌሎች ጊዜያዊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

፬. የጽሕፈት ቤቱ ዋና አድራሻ አዲስ አበባ ይሆናል፣ እንደአስፈላጊነቱም ቅርንጫፍ ይኖረዋል፡፡

፲፩. ስለገምጋሚ ተቋም

በአፍሪካ የርስ በርስ መገማገሚያ ስልት የግምገማ ዘርፎች የራስን በራስ ግምገማ አካሂዶ ሪፖርት የሚያቀርብ ከማንኛውም ወገን ነጻ የሆነ ገምጋሚ ተቋም እንዲኖር ይደረጋል፡፡

፲፪. የመተባበር ግዴታ

በዚህ ደንብ ውስጥ የተጠቀሱት ተቋማት ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ የፌዴራልና የክልል መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ሰዎች የመተባበር ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

፲፫. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሣስ ፳፫ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

(e) organize meetings and field trips of the Governing Council and receive visitors on behalf of the council;

(f) facilitate and support the work of the Technical Research Institutions;

(g) carry out other functions as may be assigned to it by the Governing Council and the Chairperson;

(h) make sure that books of accounts are kept;

3/ The secretariat shall have personnel to be assigned on the basis of ad hoc from different governmental and non-governmental institutions and other temporary employees.

4/ The secretariat's head office shall be in Addis Ababa and it shall have branch offices, if necessary.

11. *Technical Research Institution*

There shall be an independent Technical Research Institution that shall undertake research and provides a self-assessment report on the thematic areas of the African Peer Review Mechanism.

12. *Duty to cooperate*

Federal and regional authorities as well as other concerned person shall have the duty to cooperate with the institutions mentioned in this regulation in the course of carrying out their functions.

13. *Effective Date*

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 2nd day of January, 2008

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አስራ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፲
አዲስ አበባ-ጥር ፭ ቀን ፪ሺ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No. 10
ADDIS ABABA-14th January, 2008

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፩፻፵፫/፪ሺ.ህ
የኢትዮጵያ የሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ....ገጽ ፫ሺ፱፻፺፪

## CONTENTS

Regulation No. 143/2008
The Ethiopian Meat and Dairy Technology Institute Establishment Council of Ministers Regulation ...... ...........Page 3992

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፵፫/፪ሺ.ህ

## የኢትዮጵያ የሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም

## የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ «የኢትዮጵያ የሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፵፫/፪ሺ.ህ» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

፩. ‹‹የሥጋና ወተት ምርት›› ማለት የእንስሳት ምርትና ተዋፅኦን የጠቃልላል፤

፪. ‹‹የእንስሳት ምርት›› ማለት ሥጋ፣ ወተት፣ ቅቤና አይብ ማለት ሲሆን ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ምርት ብሎ የሚሰይማቸውን ያጠቃልላል።

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO.143/2008

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHEMENT OF THE ETHIOPIAN MEAT AND DAIRY TECHNOLOGY INSTITUTE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005.

1. ***Short Title***

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Meat and Dairy Technology Institute Establishment Council of Ministers Regulation No. 143/2008"./

2. ***Definitions***

In This Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "Meat and Dairy products" means products including livestock products and by-products.

2/ "Livestock Products" means meat, milk, butter and cheese, and includes other products designated by the Institute as livestock products.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.80

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁጥር ፹ሺ ፩
Negarit Gazeta P.O.Box 80,001

፫. «የእንስሳት ተዋፅኦ» ማለት እንደ ቀንድ፣ ሸኮና ፣ ደም፣ አጥንትና አንጀት የመሳሰሉ ከእንስሳት እርድ የሚገኙና ተፈላጊነት ያላቸው ተረፈ ምርቶች ሲሆኑ ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ተዋፅኦ ብሎ የሚሰይማቸውን ሌሎች ተረፈ ምርቶችን ያጠቃልላል፣

፬. «እንስሳት» ማለት ዳልጋ ከብት፣ በግ፣ ፍየልና ግመል ማለት ሲሆን ኢንስቲትዩቱ እንስሳት ብሎ የሚሰይማቸውን ያጠቃልላል፡፡

፭. «ቴክኖሎጂ» ማለት በምርምር፣ በሙከራና በአዲስ የአሠራር ስልት የተገኙና ጥቅም ላይ ሲውሉ የምርት ጥራት፣ ምርታማነትና የአሠራር ቅልጥፍናን የሚጨምሩ የአሠራር ዘዴዎች ናቸው፤

፮. «ግብዓት» ማለት የሥጋና ወተት ምርትን ምርታማነትና ጥራት ለማሳደግ ሲባል ጥቅም ላይ የሚውል ስነ-ህይወታዊ ወይም ግዑዝ ነገር ነው፤

፯. «ማቀነባበር» ማለት ማንኛውም ምርት በዓይነት፣ በይዘት ወይም በተዛማጅ ሁኔታ ቀድሞ ከነበረው እሴት ለመጨመር የሚደረግ አሠራር ነው፤

፰. «ኢንዱስትሪ» ማለት አንድን ምርት ወይም ምርቶች ለማምረት ወይም ለመፈብረክ በሚያስችል ሁኔታ የተቀናጀ ወይም የተያያዘ የሥራ መስክ ነው፤

፱. «የሚመለከታቸው» ማለት ኢንስቲትዩቱ በሚሰጠው ማንኛውም አገልግሎት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚሣተፉ፣ የሚጠቀሙ ወይም በሌላ ሁኔታ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሰዎች ያጠቃልላል፤

፲. «ክልል» ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) ላይ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፲፩. «ሚኒስቴር» ወይም «ሚኒስትር» ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፲፪. «ሰው» ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፫. *መቋቋም*

፩. የኢትዮጵያ የሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ «ኢንስቲትዩት» እየተባለ የሚጠራ) የህግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪. ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

3/ “Livestock By-Products” means by-products such as horn, hoof, blood, bone, intestine and other similar valuable by-products of slaughtered animals and includes other by-products designated by the Institute as livestock by-products.

4/ “Livestock” means cattle, sheep, goat, camel and includes other animals designated by the Institute as livestock.

5/ “Technology” means methods of work developed by research, experiment and new way of performing and when placed in practice results in the increment of production, quality, productivity and efficiency.

6/ “Input” means things of biological or material nature when used improve the productivity and quality of meat and dairy products.

7/ “Processing” means a mechanism by which the value of a product is increased in terms of type, content or the like.

8/ “Industry” means a field of work integrated or associated in a manner capable for the purpose of producing or fabricating a certain product or products.

9/ “Stakeholders” means persons, who directly or indirectly take part, benefit or in any other way are concerned with any of the services of the Institute.

10/ “Regional State’ means any regional state specified under Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, and includes the Addiss Ababa and Dire Dawa Administrations.

11/ “Ministry” or “Minister” means the Ministry or Minster of Agriculture and Rural Development respectively.

12/ “Person” mean a physical or judicial person.

3. ***Establishment***

1/ The Ethiopian Meat and Dairy Technology Institute (hereinafter referred to as the “Institute”) is hereby established as an autonomous federal government agency having its own juridical personality.

2/ The Institute shall be accountable to the Ministry.

፬. የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት

የኢንስቲቲዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት ቢሾፍቱ ከተማ ይሆናል። እንደአስፈላጊነቱም በሌሎች ቦታዎች ሞዴል ማዕከላትን ማቋቋም ይችላል።

፭. የኢንስቲትዩቱ ዓላማ

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

፩. በሥጋና ወተት ምርትና አቅርቦት ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላትን አቅም የመገንባት ፣ እና

፪. የሥጋና የወተት ምርትና አቅርቦት የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የማስቻል።

፮. የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባራት

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. በሥጋና ወተት ምርትና አቅርቦት ሥራ ላይ ለተሰማሩ ሰዎች ገበያ ተኮር የሆነ የፅንሰ ሀሳብና ተግባር ሥልጠና የመስጠት፤

፪. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሥጋና የወተት ምርት ለውጭ ገበያ የሚያዘጋጁ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ዓለም አቀፍ መስፈርት አሟልተው እንዲቋቋሙና እንዲሠሩ የቴክኒክና የሙያ ብቃት እንዲኖራቸው የማስቻል፣

፫. በአገር አቀፍ ደረጃ ለሥጋና ወተት ምርትና ግብዓት የናሙና ትንተናና የጥራት ማረጋገጫ አገልግሎት የሚሰጥ ላቦራቶሪ ማደራጀትና ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ፣

፬. የሥጋና ወተት ምርት አቅርቦትና የጥራት ደረጃን ለማሳደግ የሚያግዙ የምክርና የመረጃ አገልግሎቶችን የመስጠት፤

፭. ገበያ ተኮር የሆኑ የሥጋና የወተት ምርት ቴክኖሎጂዎች በሀገር ውስጥ ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የፍተሻ ተግባራት የማካሄድ፤

፮. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ገበያ ተኮር የሥጋና ወተት ልማትና ምርምር የሚዳብርበት ሁኔታ እንዲመቻች ማበረታታትና ድጋፍ የመስጠት፤

፯. በሥጋና በወተት ኢንዱስትሪ በተሻለ ደረጃ ላይ ከሚገኙ የውጭ ሀገር ተቋማት እና ተዛማጅ ዓላማ ካላቸው የሀገር ውስጥ ተቋማት ጋር የትብብር ግንኙነት የመመስረት፣

፰. አግባብ ላላቸው የክልል ተቋማት የቴክኒክ እገዛና ምክር የመስጠት፤

፱. ለሠልጣኞች የምስክር ወረቀት የመስጠት፤

፲. መንግሥት በሚያጸድቀው ተመን መሠረት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ክፍያ ማስከፈል፤

4. *Head Office*

The Institute shall have its head office at Bishoftu and may have Model Centers in other places, as may be necessary.

5. *Objectives*

The Institute shall have the following objectives:

1/ to build the capacity of those engaged in the production and supply of meat and dairy products: and

2/ to ensure that quality standards are maintained in the production and supply of meat and dairy products.

6. *Powers and duties of the Institute*

The Institute shall have the powers and duties to:

1/ provide market-oriented theoretical and practical trainings to those engaged in the production and supply of meat and dairy products;

2/ in cooperation with stakeholders, enable processing plants of exporters of meat and dairy products to improve their technical and professional competence so that they are constructed and operated in compliance with the requirements of international standard;

3/ establish a laboratory and provide sample analysis and quality assurance services, at a national level, relating to meat and dairy products and livestock inputs;

4/ provide consultancy and information services with a view to improving the supply and quality standards of meat and dairy products;

5/ in collaboration with stakeholders, evaluate market-oriented meat and dairy technologies before they are supplied to the domestic market;

6/ in collaboration with stakeholders, encourage and support the development and research efforts targeted to market-oriented meat and dairy products;

7/ establish relationships with foreign institutions that are in better position with regard to meat and dairy industries and local institutions having similar objectives;

8/ give technical support and advice to the relevant institutions of regional states;

9/ issue certificates to trainees;

10/ collect service fees in accordance with rates to be approved by the Government;

፲፩. የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በራሱ ስም የመክሰስና የመከሰስ፤

፲፪. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን፡፡

፯. <u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>

ኢንስቲትዩቱ፣

፩. አማካሪ ቦርድ (ከዚህ በኋላ ‹‹ቦርድ›› እየ ተባለ የሚጠራ)፣

፪. በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተር፣ እና

፫. አስፈላጊው ሠራተኞች፣ ይኖሩታል፡፡

፰. <u>የቦርዱ አባላት</u>

ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ በመንግስት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል፡፡ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል፡፡

፱. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባራት</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩. በኢንስቲትዩቱ የሥራ ዕቅዶችና ፕሮጀክቶች ላይ ይመክራል፣ ሃሳብ ያቀርባል፣

፪. የኢንስቲትዩቱን ዓላማ ለማሳካት በሚረዱ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ይመክራል ፣ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

፲. <u>የቦርዱ ስብሰባ</u>

፩. ቦርዱ በየሩብ ዓመቱ አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፡፡ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፪. ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የቦርዱ አባላት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፫. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፡፡ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፲፩. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩. ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋና ዳይሬክተሩ፣

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፤

11/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name; and

12/ perform other related activities in order to fulfill its objectives.

7. ***Organization of the Institute***

The Institute shall have:

1/ an Advisory Board (hereinafter referred to as the" Board");

2/ a Director General to be appointed by the Government upon the recommendation of the Minister; and

3/ the necessary staff.

8. ***Members of the Board***

The Board shall have a Chairperson and members to be appointed by the Government from governmental institutions and the private sector: and their number shall be fixed as necessary.

9. ***Powers and Duties of the Board***

The Board shall have the following powers and duties:

1/ deliberate on the work plans and projects of the Institute and forward recommendations thereon:

2/ deliberate on other issues and forward recommendations that help the Institute to fulfill its objectives.

10. ***Meetings of the Board***

1/ The Board shall hold a regular meeting once every quarter of the budget year: provided, however, that it may hold an extraordinary meeting whenever found necessary.

2/ There shall be a quorum where more than half of the members of the Board are present at a meeting.

3/ Decisions of the Board shall be passed by a majority vote; in case of a tie the Chairperson shall have a casting vote.

11. ***Powers and Duties of the Director General***

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Institute and shall, subject to the general directives of the Ministry, direct, administer and supervise the activities of the Institute.

2/ Without prejudice to sub-Article (1) of this Article the Director General shall:-

a. exercise the powers and duties of the Institute specified under Article 6 of this Regulation;

ለ) የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ ዓላማ ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) በኢንስቲትዩቱ የሥራ ፕሮግራምና በጀት መሠረት ክፍያዎችን ይፈፅማል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

ሰ) በሚኒስቴሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

፫. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

፲፪. በጀት

የኢንስቲትዩቱ በጀት በፌዴራል መንግሥት ይመደባል።

፲፫. ስለሂሳብ መዛግብት

፩. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።

፪. የአንስቲቲዩቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

፲፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ፣ ጥር ፮ ቀን ፪ ሺህ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

b. employ and administer the employees of the Institute in accordance with directives to be approved by the Government following the basic principles of the federal civil service laws;

c. prepare and submit the work program and budget of the Institute to the Ministry, and implement the same upon approval;

d. effect payments in accordance with the approved budget and work program of the Institute;

e. represent the Institute in all its dealings with third parties;

f. prepare and submit to the Ministry the performance and financial reports of the Institute; and

g. carry out other duties given by the Ministry.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officials and employees of the Institute to the extent necessary for the effective performance of the activities of the Institute.

12. ***Budget***

The budget of the Institute shall be allocated by the Federal Government.

13. ***Books of Accounts***

1/ The Institute shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Institute shall be audited annually by the Auditor General or by auditors designated by him.

14. ***Effective Date***

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta

Done at Addis Ababa, this 14th day of January, 2008.

**MELES ZENAWI**

**PRIME MINISTER OF THE**

**FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF**

**ETHIOPIA**